በመካነ ሰላም መድኃኔዓለም የሐመረ ኖኅ ሰንበት ት/ቤት

# አራራት

አራራት የኖኅ መርከብ ከጥፋት ውሃ በኋላ ያረፈበት የተራራ ስም ነው።

የሐመረ ኖኅ የሰንበት ት/ቤት የሥነ ጽሑፍ ክፍል ይህችን በየ3ወሩ አንድ ጊዜ እየታተመች የምትወጣ ጽሑፍ አራራት በማለት የሰየመውም በዚህ ምክንያት ነው።

*«በዘመን የቀደሙ ሰዎችን አስተውሉ በእግዚአብሔር  አምኖ ያፈረ ማነው? እወቁ እሱን በመፍራት መከራውንም የታገሠ በመከራ እንደጣለው የቀረ ማነው። ለምኖትስ ቸል ያለው ማነው። እግዚአብሔር ይቅር ባይ ነውና ርኅሩኅ ነውና ኃጢአትን ይቅር ይላል ከመከራም ቀን ያድናል።» ሲራክ ምዕራፍ 2፤10*

## <u>ዶግማና ቀኖና</u>

ትምህርተ ሃይማኖት (የሃይማኖት ትምህርት) በሁለት ይከፈላል። ይኸውም

1ኛ. ዶግማ

2ኛ. ቀኖና በሚል ነው።

ቀኖና ደግሞ ቃሉ የግሪክ ሲሆን ሥርዓት ማለት ነው። ከነዚህ ከሁለቱ ዶግማ ወይም እምነት አይጨመርበትም፣ አይቀነስለትም፣ አይሻሻልም፣ ችግርና ፈተናም ቢመጣ እስከ ሞት ድረስ አጥብ ቀን የምንይዘው ነው። ለምሳሌ ያህል ይህን ዓለም ካለመኖር ወደ መኖር አምጥቶ የፈጠረ ቢመረምር እንጂ የማይመረመር ሁሉን ቻይ አምላክ የሚሳነው ነገር የሌለ ፈጣሪ፥ የሰማይና የምድር ባለቤት የሠራዊት ጌታ ሕያው እግዚአብሔር ነው።

እግዚአብሔር (ፈጣሪ) የአካል ሦስትነት አለው። በመለኮትና በመፍጠር በሥልጣን በፈቃድ ግን አንድ ነው።

በሦስትነቱ አብ፥ወልድ፥መንፈስ ቅዱስ ሲባል በአንድነቱ አንድ መለኮት አንድ እግዚአብሔር ይባላል። በአዳም ምክንያት ከመጣው የዘለዓለም ሞትና ከዲያብሎስ ባርነት ነፃ የወጣነው ከሦስቱ አካላት በአንደኛው አካል ማለትም በወልድ በአምላካችን በኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ይህ ዶግማ ወይም እምነት ይባላል።

ቀኖና ግን በአምላካችን በኢየሱስ ክርስቶስ አምነው ያደጉ ክርስቲያኖች የሚመሩበት ሥርዓት ስለሆነ፣ በሃይማኖ ትአባቶች ወይም በቅዱስ ሲኖዶስ አማካኝነት እንደጊዜው ሁኔታ የሚሻሻል በመሆኑ የሚጨመርበት የሚቀነስለት ነው። ለምሳሌ ያህል እኛ ኦርቶዶክሳውያን ስንጠመቅ ሴት በሰማንያ ወንድ በአርባ ቀናችን ነው። የተወለዱት ሕጻናት ሴቷ ሰማንያ ወንዱም አርባ ቀን ሳይሞላቸው ቢታመሙና በሽታው አስጊ ከሆነ በ10፥ በ20፥ በ30 ... ቀናቸው መጠመቅ ይችላሉ ቀኖና ነውና። በቤተ ክርስቲያናችን የቀዳስያን ብዛት መነሻው አምስት ነው። ምናልባት ከአምስቱ አንዱ፥ ሁለቱ፥ ሦስቱ ቢታጡና ሌላም ተፈልጎ እስከ መጨረሻ የማይገኝ ከሆነ ከአቅም በላይም የሆነ ችግር ከገጠመ ሁለቱ ወይም አንዱ ብቻ ቀድሶ ማቁረብ ይችላል። ቀኖና ነውና። በቤተ ክርስቲያናችን ታቦት ሲወጣ ቤተ ክርስቲያኑን (ወደ ገጽ 3 ይዞራል)

## <u>በዓለ ሃምሳ (ጰራቅሊጦስ)</u>

ከኤማሁስ ተመልሰው
በኢየሩሳሌም ተቀምጠው
ሲጠብቁ ከልብ ፀንተው፤
የተሰፋው ቃል ዕውን ሆኖ
ወረደ ተከፋፍሎ
በእሳት አምሳል ተመስሎ።
መቼ ሆነና የጉሽ ጠላ
አድሮ ውሎ የሚጣላ፤
ነበረ እንጂ መንፈስ ቅዱስ
ሕይወት ሰጥቶ የሚፈውስ
ኃይልን አድሎ ልብ የሚያድስ።
ጴጥሮስ አትፍራ ተመላለስ
በአንተ ላይ አድሯል መንፈስ ቅዱስ፤
ያለ ታንኳ ተራመደ በባሕሩ
ዓለም ይግባው ምስጢሩ፤
መንፈስ ቅዱስ ሲያበረታ
ሐዘንን አጥፍቶ ሲሆን አለኝታ፤



ፍርሃትን አስወገዶ
ድፍረትን አለማምዶ
በከሃዲዎች ፊት መቆምን አስወድዶ፤
ኃይልን ሊሰጥ ለወገኑ
ቃሉን አጥተው ለመከኑ፤
ጉስቁሉናቸው ሊጠፋ
ሊታደላቸው የጽድቅ ተስፋ
በክርስቶስ ሊታመኑ
ቀለው ላይገኙ ሲመዘኑ
በክርስትናቸው ሊታወቁ
በምግባራቸው ሊደምቁ
ሊቀርላቸው መናቁ
የተሰፋው ቃል ዕውን ሆኖ
ወረደ ተከፋፍሎ (ወደ ገጽ 4 ይዞራል)

## <u>ይህን ያውቁ ኖሯል?</u>

በዚህ ርዕስ ሥር በተከታታይ ከክርስቶስ ልደት ጊዜ ጀምሮ እስከ አሁን ዘመናችን ድረስ በቤተ ክርስቲያናችንና በሀገራችን የተፈጸሙ ዓበይት ክንዋኔዎችን በአጭሩ ለማስገንዘብ እንሞክራለን።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደዚህ ዓለም መጥቶ በቤተልሔም በተወለደ ጊዜ በኢትዮጵያ ነግሦ የነበረው ንጉሥ ባዜን ይባላል። ይህ ንጉሥም ለጌታችን መባን ለማቅረብ ከሄዱት ሰብአ ሰገል መካከል አንዱ ነው ተብሎ ይነገራል፤ ለዚህም ነው በሚሳሉ ስዕሎች ላይ ከሰብአ ሰገል መካከል አንዱ ጠቆር ያለ መልክ ያለው።

———//———

የመጀመሪያው ኢትዮጵያዊ ክርስትናን የተቀበለው በመጀመሪያው ክፍለ ዘመን፤ ክርስቶስ በዐረገ በዓመቱ ማለትም በ 34 ዓ.ም በሐዋርያው በፊልጶስ እጅ ነበር (ሐዋ. 8፤26-40)። ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ስለ መንፈስ ቅዱስ መውረድ በተናገረበት ድርሳኑ መንፈስ ቅዱስ በቅድስቲቱ ከተማ በወረደበት ቀን ኢትዮጵያውያንም እንደነበሩ ጽፏል። ይሁን እንጂ የክርስትና እምነት የሀገራችን ዋና እምነት የሆነው በ4ኛው ክፍለ ዘመን በአብርሃ እና አጽብሐ ዘመነ መንግሥት ከ298-336 ነው። የመጀመሪያውም ሊቀ ጳጳስ ፍሬ ምናጦስ ወይም ከሣቴ ብርሃን ነበር (ወደ ገጽ 2 ይዞራል)

### WALKING BY FAITH

The Sacred Scriptures frequently speak about the "Christian walk" as a description of believers' behavior. For example, we are told to walk as children of light, walk in the truth, walk according to the Spirit, and walk in love. St. Paul's Letter to the Colossians 2:6 uses this expression to give us an important command: *"Therefore as you have received Christ*

*Jesus the Lord, so walk in Him."* The question we must ask is, What does it mean to "walk in Christ"?

Here, the word in does not have a literal usage, like "the hammer is in the toolbox." Rather, it refers to a vital relationship—a union between the believer and the Lord. Just as a wedding marks the beginning of a new relationship for a man and a woman, receiving Christ as Savior commences an intimate fellowship between the Lord and His follower. What God desires is not simply to forgive sins, but to develop a close and ever-deepening personal relationship with each of His children. He wants us to realize that the Son of God is the source of everything—Jesus Christ is to the believer what blood is to the human body: indispensable to life.

Therefore, "walking in Christ" refers to a dynamic relationship with the Lord Jesus Christ. Just as it is impossible to walk while standing still, believers are either moving forward in their Christian life or falling backward. The key for how to make progress is found in that same Colossians verse: ***"As you have received Christ Jesus the Lord, so walk in Him."*** How did you and I receive Christ? By faith! In Holy Baptism, in order to be born again, we trusted the testimony of the Word of God. The Christian life is to be "walked"—or lived out—in the same way.

Most people are guided by their natural senses, but that is not effective because from our human viewpoint, we are unable to see the big picture. Instead, Almighty God our heavenly Father wants us to trust Him daily for whatever need we may have. That is why followers of Jesus Christ are to ***"walk by faith, not by sight"*** (2 Corinthians 5:7). We must take the first step by faith, and then another, not knowing exactly where it will lead us, but trusting that our omniscient, loving Almighty God has our best interest in mind. To walk in faith means having a personal relationship with Jesus Christ that results in trusting Him for every circumstance of life. When we consistently live with that kind of confidence in the Lord, we will believe He will do what is right and what is for our benefit every time, without exception.

## አጫጭር ዜናዎች

### ባለፉት 3 ወራት የተካሄዱ ክብረ በዓላት

- በአለፈው የዐቢይ ጾም ወቅት በየምሽቱ የሠርክ ጸሎትና ትምህርት ሲሰጥ ሰንብቷል። በየዕለቱም ብዙ ምዕመናን የተካፈሉ ሲሆን በአጠቃላይ መርሐ ግብሩም ምዕመናን እንደተደሰቱ ገልጸዋል።

- የመድኃኔዓለም ጥንተ ስቅለቱ በደመቀ ሁኔታ መጋቢት 27 ቀን ብጹዕ አቡነ ዜና ማርቆስ፣ ብጹእ አቡነ መልከ ጼዴቅ እንዲሁም ከተለያየ ከተማ የመጡ ካህናት፣ መዘምራንና ምዕመናን በተገኙበት ተከብሮ ውሏል።

- ታላቁ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ በዓል ሚያዚያ 19 ቀን እጅግ ብዙ ምዕመናን በተገኙበት ተከብሯል። በዕለቱም ያሬዳዊ ዜማና በዓሉን የተመለከቱ መዝሙራት ከቅዳሴ በፊትና በኋላ ቀርቧል።

- ሰኔ __ ቀን ፳፻፫ ዓ.ም. በተከበረው የጰራቅሊጦስ በዓል ላይ የቤተ ክርስቲያናችን አገልጋይ የሆነው ዲያቆን ወንድምነህ _____ የቅስናን መዓረግ ከብጹዕ አቡነ መልከጼዴቅ ተቀብሏል። በዚሁ ዕለት በ፳፻፫ ዓ.ም. ትምህርታቸውን ከሁለተኛ ደረጃ ለአጠናቀቁ ወጣቶች ጸሎተ ቡራኬና ስጦታ ተበርክቶላቸዋል።

## ይህን ያውቁ ኖሯል?

(ከገጽ 1 የዞረ)

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ለመጀመሪያ ጊዜ ከሀገራችን ውጭ የተመሠረተችው በ4ኛው ክፍለ ዘመን በቅድስት ሀገር ኢየሩሳሌም እንደነበር በኢየሩሳሌም የነበረው የላቲን ቤተ ክርስቲያን አባት ቅዱስ ጅሮም ጽፎታል። እነዚያ ደጋግ አባቶቻችን ወደ ኢየሩሳሌም በመጓዝ ጌታችን ኢየሱስ ክርሰቶስ ወደዚህ ዓለም መጥቶ በተወለደበት በቤተልሄም፣ በተጠመቀበት በዮርዳኖስ፣ በተሰቀለበት በቀራንዮ፤ እንዲሁም በጎልጎታ፣ በጌቴሰማኒ፣ በጽዮን ተራራ በሌሎችም ቦታዎች ገዳማትን መሥርተው ለእኛ አስተላልፈዋል።

—//—

በሦስተኛው ክፍለ ዘመን የአክሱም መንግሥት በዘመኑ በዓለም ላይ ከነበሩት ኃያላን መንግሥታት ተብለው ከሚቆጠሩት ከሮም ከቻይና እና ፐርሺያ አንዱ ነበር።

—//—

በእልአሜዳ ዘመነ መንግሥት በ472 ዓ.ም. አካባቢ የሁለት ባሕርይን እምነት አንቀበልም ያሉ ዘጠኝ የቤተክርስቲያን አባቶች ወይም ተስዐቱ ቅዱሳን በመባል የሚታወቁት ከቊስጥንጥንያ አሁን ቱርክ ከሚባለው፣ ከሶርያና ከሌሎች የሮማ ግዛቶች ወደ ኢትዮጵያ ተሰደው መጡ። የእነዚህ አባቶች ወደ ኢትዮጵያ መምጣት ለታላላቅ ገዳማት መመሥረት፣ ብዙ የቅዱሳት መጻሕፍት ወደ ግእዝ መተርጐም፣ የጣያት አምልኮ እንዲቀርና የክርሰትና እምነት ወደ ሌሎች የኢትዮጵያ ግዛቶች እንዲያውም አልፎ ተርፎ ከቀይ ባሕር ባሻገር ወደ የመን እንዲሰፋፋ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርገዋል።

—//—

በ516ዓ.ም. አካባቢ በዐፄ ካሌብ ዘመነ መንግሥት ከቀይ ባሕር ባሻገር ባለው የኢትዮጵያ ግዛት በነበረው ደቡብ ዐረብ ክፍል (የመን) በአካባቢው የሚኖሩ አይሁዳውያን በዱዋ ኑዋስ መሪነት ዛፋር ላይ የሚገኙት ክርስቲያኖች ተሰብስበው በቤተ ክርስቲያን ሲጸልዩ እንዳሉ ካቃጠሉአቸው በኋላ ወደ ናግራን በማምራት በዚያ ከሰፈረው የኢትዮጵያ ጦር ገጥመው ከተማውን ለመያዝ ባይችሉም ከፍተኛ ጉዳት አደረሱ። ዐፄ ካሌብም 120,000 የሚሆን ጦር ይዘው ከአዱሊስ ወደብ አካባቢ ተነሥተው ወደ ናግራን ዘምተው ጦርነቱን ቢያሸንፉም ዱዋ ኑዋስ አመለጠ። ካሌብም በዛፋር የፈረሱትን አብያተ ክርስቲያናት እንደገና አሠርተው፣ በቂ ጦር ትተው ወደ አኩሱም ተመለሱ። ይሁን እንጂ የንጉሡን መመለስ የሰማው ዱዋ ኑዋስ እንደገና እየወረረ በዚያ በሰፈረው የኢትዮጵያ ጦር ላይ አደጋ ማድረስ ጀመረ። በዚህ የተነሣ ዐፄ ካሌብ ከ2 ዓመት በኋላ ተመልሰው ወደ የመን ዘመቱ። ዱዋ ኑዋስ እንደለመደው የኢትዮጵያ ጦር ከባሕር እንዳለ ወደ መሬት እንዳይጠጋ ሲዋጋ በጀርባ በየመን የሰፈረው ጦር ከቦት ማምለጫ ስላሳጣው ከመማረክ ብሎ ወደ ባሕሩ ገብቶ ከብዙ ሠራዊቱ ጋር ሞተ። ዐፄ ካሌብ ከድሉ መልስ በኋላ መንግሥታቸውን ትተው ፣ ሥርዓተ ንግሥና የተቀዳጁበትን ዘውድ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በተቀበረበት በጎልጎታ (ኢየሩሳሌም) እንዲቀመጥላቸው ልከው፣ የቀረ ዘመናቸውን በብሕትውና በአባ ጴንጤሌዎን ገዳም ኖረው በ70 ዓመታቸው ዐረፉ። እኚህ ታላቅ ንጉሥ በየመን ሥቃይ ለደረሰባቸው ክርስቲያኖች በመድረሳቸውና የቀረ ዘመናቸውን በፍጹም ምናኔ

በማሳለፋቸው፣ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እንዲሁም በካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ተብለዋል። በግሪክ ቤተ ክርስቲያንም የናግራን ሰማዕታት ዕለት በሚከበርበት ቀን ዐፄ ካሌብም ታስበው ይውላሉ። በዓሉም እንደ አውሮጳውያኑ አቈጣጠር በየዓመቱ ጥቅምት 27 ቀን ነው።

*በእደ ማርያም እጅጉ ረታ*

## ጠይቁን እንመልሳለን

ይህ ዓምድ ከምዕመናን የሚጠየቁ ጥያቄዎችን የምናብራራበት፣ መልስ የምንሰጥበት ነው።

### ፋሲካ ማለት ምን ማለት ነው?

(ጠያቂ አቶ ናትናኤል)

በዕብራይስጥ ፋሲካ «ፓሳህ» ይባላል (ዘፀ 12) እንደምናነበው የእስራኤል ልጆች ፋሲካን ያዘጋጁት አሥረኛ መቅሰፍት ሆኖ በታዘዘው ሞተ-በኩር በግብጻውያን ላይ ሲያልፍ እነሱንም የሞት መልአክ እንዳይቀጣቸው የፋሲካን በግ አርደው ያከበሩት የእግዚአብሔር በዓል ነው። ፋሲካን ያከበሩት ከነፃነት በፊት ነው። በዓሉንም ከነፃነት በኋላ በየዓመቱ በአሥራ አራተኛው ቀን ያከብሩት ነበር። (ዘፀ 16፥6 ዘፀ 12፥1-3) ከዚያም እስከ አንድ ሳምንት ድረስ የቦካውን ነገር ለመብላት ስላልተፈቀደላቸው አንድ ሳምንት የቂጣ በዓል ያከብራሉ። ኢየሱስ ክርስቶስ የተሰቀለበት ሳምንት የፋሲካ ሳምንት ነበር (ሉቃ 22፥14-16 ዮሐ 18፥38-40) ክርስቶስ ንጹሕ የእግዚአብሔር በግ ሆኖ ደሙን ስለአፈሰሰልን (ፋሲካችን ክርስቶስ) ተባለ። (1ቆሮ 5፥7 1ጴጥ 1፥18-19) ስለዚህ የክርስቶስ ትንሣኤ በዓለ ፋሲካ ተብሎ ይጠራል። በአጠቃላይ ፋሲካ ማለት መሻገር ማለት ነው።

## ከቅዳሴ መጻሕፍት

(ከቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ቅዳሴ የተወሰደ)

የተሰበሰብን እኛም የማይታመም የርሱን ሕማሙን እንናገራለን፤ የማይሞት የርሱን ሞቱን እንናገራለን። ከደቀ መዛሙርቱ ጋራ በተቀመጠባት በዚያች ሌሊት በአባቱ ፈቃድ በራሱም ፈቃድ ሰውነቱን ለሞት ሰጠ።

ሁሉን የያዘውን ያዙት፤ ሁሉን የሚገዛውን አሰሩት፤ የሕያው የአምላክን ልጅ አሠሩት፤ በቍጣ ጐተቱት በፍቅር ተከተላቸው፤ በሚሸልተው ፊት እንደማይናገር እንደ የዋህ በግ በኋላቸው እየተከተለ ወሰዱት።

ሊቃነ መላእክት በመፍራትና በመንቀጥቀጥ ከፊቱ የሚቆሙለትን በአደባባይ አቆሙት፤ ኃጢአትን ይቅር የሚለውን ኃዋእ አሉት፤ በመኳንንት በሚፈረደው በርሱ ፈረዱበት።

ለሱራፌል ዘውድ የሚያቀዳጃቸውን የእሾህ ዘውድ አቀዳጁት። ለኪሩቤል የግርማ ልብስ የሚያለብሳቸውን ለመዘበት ቀይ ግምጃ አለበሱት።

ኪሩቤል በእሳት ክንፍ ተሸፍነው ከፊቱ የሚሰወሩለትን እርሱን ክፉ ባሪያ እጁን አጽንቶ ፊቱን ጸፋው።

የመላእክት ሠራዊት በፍጹም መደንገጥ ለሚሰግዱለት እየዘበቱበት በፊቱ ተንበረከኩ።

ይህን ያህል ትህትና እንደምን ያለ ትህትና ነው። ይህን ያህል ትዕግሥት እንደምን ያለ ትዕግሥት ነው። ይህን ያህል ዝምታ እንደምን ያለ ዝምታ ነው።

ይህን ያህል ቸርነት እንደምን ያለ ቸርነት ነው። ይህን ያህል ሰውን ማፍቀር እንደምን ያለ ፍቅር ነው።

ፍቅር ያምላክን ልጅ ከዙፋኑ ሳበው እስከ ሞትም አደረሰው። በደል የሌለበትን እንደ በደለኛ ሰቀሉት። ሕይወትን የሠራውን ከበደለኞች ጋራ ቆጠሩት።

አዳምን የፈጠሩ እጆች በመስቀል ቀኖት ተቸነከሩ ወዮ። በገነት የተመላለሱ እግሮች በመስቀል ቀኖት ተቸነከሩ ወዮ።

በአዳም ፊት የሕይወት መንፈስን እፍ ያለ አፍ ከሐሞት ጋራ የተቀላቀለ የኮመጠጠ መጻጻን ጠጣ ወዮ።

የወልድን መከራውን የሚናገር ምን አፍ ነው፤ ምን ከንፈር ነው፤ ምን አንደበት ነው።

የፍቅር የጌታ ሕማማት በተነገረ ጊዜ ልብ ይለያል ኅሊናም ይመታል ነፍስም ትንቀጠቀጣለች ሥጋም ይደክማል።

የማይሞተው ሞተ ሞትን ይሽረው ዘንድ ሞተ ሙታንን ያድናቸው ዘንድ ሞተ።

## The Anaphora of St. John Chrysostom

And we, who have gathered together, proclaim the sufferings of him who does not suffer and proclaim the death of Him who does not die. In the same night when He sat with His disciples He gave His soul over to death with the will of His Father and in His own good pleasure.

They took hold of Him who takes hold of all, bound the ruler of all and shackled the Son of the living God ; they drew Him in wrath and He followed them in love, they took Him and He followed them like a meek sheep which is dumb before its shearers.

They caused to stand in the court Him, before Whom stand archangels in fear and trembling. He who forgives sins, was accused as a sinner by them, the Judge of judges was judged by them.

Him, Who crowns seraphim with a coronet, they crowned with a crown of thorns. Him, Who clothes cherubim with garments of might, they clothed with a scarlet robe to mock Him.

A wicked servant strengthened his hand to strike the face of Him from Whose face the cherubim are hidden being covered with wings of fire.

They knelt before him, mocking Him Whom the hosts of angels worship in great fear.

Oh what humility is this! Oh what patience is this! Oh what a silence is this!

Oh what a kindness is this! Oh what a love of man is this!

Love drew down the Son of God from His throne and brought Him unto death. Him, Who had no wickedness, they crucified as wicked. Him, Who is the maker of life, they numbered with the wicked.

Oh the hands which formed Adam were nailed with the nails of the cross. Oh the feet which walked in the garden were nailed with the nails of the cross.

Oh the mouth which breathed the spirit of life into the nostrils of Adam drank vinegar mixed with gall.

What mouth, what lips, what tongue can express the sufferings of the Son?

The heart is broken, the mind is perplexed, the soul trembles and the flesh is weary when the

sufferings of the Beloved are mentioned.

The Immortal died: died to destroy death, died to quicken the dead.

## ዶግማና ቀኖና

(ከገጽ 1 የዞረ)

የሚዞረው ሦስት ጊዜ ነው ችግር ከአለ አንድ ጊዜ ብቻ ዙሮ መግባት ይችላል። ቀኖና ነውና በአጠቃላይ ሥርዓትን በተመለከተ ቀኖና ይባላል።

እምነትና ሥርዓትን ቅዱስ ጳውሎስ ለይቶ አስተምሮናል ለምሳሌ ያህል በቆላስይስ ሰዎች 2. ቁ. 5 ላይ እንዲህ ይላል። «በሥጋ ምንም እንኳ ብርቅ በመንፈስ ከእናንተ ጋር ነኝና ሥርዓታችሁንም በክርስቶስም ያለውን የእምነታችሁን ጽናት እያየሁ ደስ ይለኛል» በዚህ ምንባብ ውስጥ በክርስቶስ የሆነው እምነት ዶግማ ሲባል ሥርዓት ብሎ የጠራው ቀኖናን ነው። ሰለቀኖና (ስለሥርዓት) ቅዱስ ጳውሎስ ደጋግሞ ጽፏል። ከጻፈውም ውስጥ፥

1. «ነገር ግን ሁሉ በአገባብና በሥርዓት ይሁን።» 1ቆሮ. 14፥40

2. «ወንድሞች ሆይ ከእኛ እንደተቀበለው ወግ ሳይሆን ያለ ሥርዓት ከሚሄድ ወንድም ሁሉ ትለዩ ዘንድ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እናዛችኋለን። እኛን ልትመስሉ እንዴት እንደሚገባችሁ ራሳችሁ ታውቃላችሁና» 2 ተሰ. 3፥6-7 ቀኖና (ሥርዓት) የሚወስነው በሃይማኖት አባቶች እንደሆነና ወንጌልን የሚያስተምር ሰው ለሚያስተምራቸው ክርስቲያኖች በሃይማኖት አባቶች የተወሰነውን ቀኖና ማስተማርና መስጠት እንዳለበት መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ሲል ያስረዳል።

በከተማዎችም ሲዞሩ በኢየሩሳሌም የነበሩት ሐዋርያትና ሽማግሌዎች የቆረጡትን (የወሰኑትን) ሥርዓት ይጠብቁ ዘንድ ሰጧቸው። አብያተ ክርስቲያናትም በሃይማኖት ይበረቱ ነበር፥ በቁጥርም ዕለት ዕለት ይበዙ ነበር።» ይላል። የሐዋ. 16፥4-5 በዚህ የእግዚአብሔር ቃል መሠረት ቅዱስ ጳውሎስ ደርቤንና ልስጥራን በተባሉ ቦታዎች ለነበሩ ክርስቲያኖች ወንጌልን ከሰበከ በኋላ ሐዋርያት የወሰኑትን ቀኖና (ሥርዓት) እንደሰጣቸው እናያለን። ይህም ሥርዓት በቁጥር አምስት ላይ እንደምናየው አብያተ ክርስቲያናት በሃይማኖት (በዶግማ) እንዲበረቱ፥ በቁጥርም ዕለት ዕለት እንዲበዙ እንዳደረገ እንረዳለን። ስለዚህ ቀኖና ወይም ሥርዓት ቤተ ክርስቲያንን ይጠቅማል እንጂ አይጎዳም። በመሆኑም ዶግማንና ቀኖናን ወይም እምነትንና ሥርዓትን ጎን ለጎን ይዞ መጓዝ ሐዋርያትን መከተል እንጂ ወደ ኋላ ተመልሶ አይሁድን መከተል አይደለም። እንግዲህ ሥርዓተ ቤተክርስቲያንን የሚቃወሙ ሰዎች ሁሉ፥ የሚቃወሙት በቀኖና (በሥርዓት) የሚመሩትን ክርስቲያኖች ሳይሆን የእግዚአብሔር ቃል የሆነ መጽሐፍ ቅዱስን በመሆኑ እንዳይሳሳቱ አደራ እንላለን። (ከመለከት)

## በዓለ ሃምሳ (ጰራቅሊጦስ)

(ከገጽ 1 የዞረ)

በእሳት አምሳል ተመስሎ
መንፈስ ቅዱስ ሕይወት ሆኖ
የታመመውን ሊፈውሱ
አሮጌውን ሊያድሱ
በትምህርታቸው ሊያንጹ
ጠማማውን ሊገስፁ
በምስጢረ ጥምቀት ሊያከብሩ
ዕውሩን ሊያበሩ
ዓይንን ሊፈጥሩ በግንባሩ
የመንፈስ ቅዱስን ኃይል ሊናገሩ
በዓለም ዙሪያ ሊመሰክሩ
ተነሱ ሐዋርያት እየዘመሩ
ለስሙ በድንጋይ ሊወገሩ
ሥጋቸውን ክደው ለነፍሳቸው ሊያድሩ።
የተሰፋው ቃል ዕውን ሆኖ
ወረደ ተከፋፍሎ
በእሳት አምሳል ተመስሎ
መንፈስ ቅዱስ ሕይወት ሆኖ

ኃይለ መስቀል ተሰፋዬ



## ደብረ ታቦር

ሦስቱን አስከትሎ ደቀ መዛሙርት
ወደ ታቦር ወጣ ጌታ ለፀሎት
መልኩ ተለውጦ እንደ ፀሐይ አብርቶ
ልብሱም እንደ ብርሃን አንፀባርቆ ነጥቶ
ሙሴና ኤልያስ የብሉይ ቅዱሳን
በግራና በቀኝ ሲያናግሩት ጌታን
አዩ መሰከሩ በታቦር ተራራ
ጴጥሮስ ዮሐንስ ያዕቆብም በተራ
ጴጥሮስም ጌታውን ሊያስፈቅድ ተጣራ
መቆየት መረጠ በዚያ በተራራ
ፈቃድህ ከሆነ ሦስት ድንኳን ብንሠራ
እያለ ሲናገር ብሩሁ ደመና መጥቶ ጋረዳቸው
እጅግ የሚያስፈራ ድምፅም ከደመናው
በእርሱ ደስ የሚለኝ ልጄ የምወደው
ብሎ መሰከረ እርሱን ስሙት ይህ ነው
ሙሴና ኤልያስ ሰማያውያን ነፍሳት
ከምድራዊ ሰዎች ከሦስቱ ሐዋርያት
የተገናኙበት አምላካዊ ግብር
በታቦር ላይ ታየ መለኮታዊ ክብር

(ከሔርሚላ ካሣ)

## መጪ ዝግጅቶች

- የቅዱስ ገብርኤል በዓል በሲያትል በ July 26th ቀን ይከበራል።

- የፍልሰታ ጾም በነሐሴ 1 (August 7th) ይገባል። በየዕለቱ የጠዋት፣ የማታ ጸሎትና ትምህርት ይኖራል።

- የደብረ ታቦር በዓልን በደመቀ ሆኔታ ለማክበር የሐመረ ኖኅ ሰንበት ት/ቤት ለየት ያለ ዝግጅት ይዞ ለመቅረብ በዝግጅት ላይ ነው። ወቅቱ ሲደርስ ዝርዝሩን ያስታውቃል። ስለዚህ ያንን ቀን ጌታችን ክብሩን በደብረ ታቦር ተራራ ላይ የገለጠበትን በአንድነት ሆነን እንድናከብር ቀጠሮአችሁ ከእኛ ጋር ይሁን እንላለን።

አስተያየትና ጥያቄ ካላችሁ በቤተ ክርስቲያኒቷ የአስተያየት መስጫ ያኑሩልን። ወይም ደግሞ በሚከተለው የሥነ ጽሑፍ ዝግጅት ክፍል ኢሜይል hamere_noh@yahoo.com ይላኩልን።

**የቤተ ክርስቲያን መደበኛ አገልግሎቶች**

- ዘወትር እሁድ ጠዋት ከ7:00 - 12:00 የቅዳሴ፣ ስብከትና መዝሙር አገልግሎት ይካሄዳል።

- ከ12:15 - 1:00 በሰንበት ት/ቤት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናትና የመዝሙር መርሐ ግብር ይካሄዳል።

- ዘወትር ዓርብ ማታ ከ6:00 - 8:00 የሠርክ ጸሎትና የመጸሐፍ ቅዱስ ትምህርት ይካሄዳል።

- ለተለያዩ የቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ አገልግሎት፤ የክርስትና፣ የፍትሐት አገልግሎትን ለምትሹ በ (510) 336-1168 ደውለው ያነጋግሩን።

«ያማረ ቃል የማር ወለላ ነው፤ ለነፍስ ጣፋጭ ለአጥንትም ጤና ነው።»
(ምሳሌ 16፥24)